# የሰላማዊ፡ሰልፉ፡ችን፡ጠለፋ፡በዋሽንግተን፡ዲ፡ሲ፤

**"ይኸን፡ምልክት፡በፊደሎች፡አናት፡ላይ፡እንሆ!፡ማጥበቂያ፡አድርገናል።**

**በዜናማርቆስ፡መርሐ፤ ካናዳ።**
**እ.ጠማር፤ zienamarqos@yahoo.com**

እንደዚህ፡ዓይነቱ፡ውዝግብ፡ከ፲፰፡ዓመታት፡ወያኔአዊ፡አምባ፡ገነን፡የጭቆና፡ወረራ፡እና፡አገዛዝ፡በኋላ፡በመነሣቱ፡ከልብ፡እናዝናለን።የጋዜጠኝነት፡ሥነ፡ምግባር፡በጐደላቸው፡እና፡በኢትዮጵያ፡እና፡ሕዝቧ፡ችግር፡በእሚነግዱ፡ይሉኝታ፡ቢስ፡ወገኖቻችን፡መሆኑም፡እያሰሳጨን፡ነው።እናም፤የሀገር፡ፍቅር፡ነፉስ፡ድምፅ፡ዜና፡አዘጋጆች፡አቶ፡ንጉሤ፡ወልደ፡ማርያም፡እና፡ሐኪም፡በላይ፡ወልደ፡ኢየሱስ፤መለሰ(ለገሠ)፡ዜናዊን፡በማሞካሸት፡ኢትዮጵያውያት፡እና፡ኢትዮጵያውያን፡ለሀገር፡መዘረፍ፡እና፡ለኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡መብት፡መገፈፍ፡ለጂ፡ሣያ፡በፔልሲቫኒያ፡ተሰብሳቢ፡ኃያላን፡መንግሥታት፡መሪዎች፡አቤቱታ፡ለማቅረብ፡**አረንጓዴ፤ቢጫ፡ቀይ፡ዓላማቸውን**፡ተላብሰው፡በመውጣታቸው፡አፌዙሳቸው።ሣቁሳቸው።በዓላማችን፡ለባሽ፡ባለ፡ታሪኮችም፡ኮርተናል።ለወደፊቱም፡እንኮራለን።ፌዙ፡እና፡ሣቁ፡ግን፡በንጉሤ፡እና፡በበላይ፡መሆኑን፡ጎሊና፡ያለው፡ይገምተው።ከወያኔው፡መንግሥት፡እንደራሴ፡ጽሕፈት፡ቤት፡(ኤምባሲ)፡ሠራተኞች፡ጋራ፡ተባብረው፡የአምባ፡ገነን፡ወያኔን፡የሣጥናኤል፡ሰንደቅ፡ዓላማ፡በእሚከሰርሰት፡ቀን፡ለምን፡አልተገኛችሁም፡እያሉ፡ኢትዮጵያውያትን፡እና፡ኢትዮጵያውያንን፡በዜናቸው፡ተዛልፈዋል።በዚህ፡እነሱን፡አኃላጭ፡አጻጻፉ፡ችንም፡ሽንጣቸውን፡ገትረው፡ከእሚነዘዝንዙት፡ማኅበረ፡ቅዱሳን፡ወይም፡በመሰላቸው፡ፈጥረው፡እንደ፡እሚአዳብሉን፡በመገንዘብም፡ነው።ለከሀዲ!፡ምን፡ግድ፡አለን፡እና!!።አገር፡እና፡ወገንን፡ንቆ፡ለጥቅሙ፡የእሚያድርን፡ማግለል፡አያስኮንንም።

**"እናንተ፡ወያኔ፡ወያኔ፡የምትሉ፡ሁሉ፡ይኸን፡ወያኔ፡አሳባላችሁን፡አቁሙ።ወያኔ፡እኮ፡ሥራውን፡እየሠራ፡ነው።እና፤ተውት፡ይሥራበት"**።በማለት፡መልእክታቸውን፡በነፉስ፡ድምፃቸው፡ዜና፡አስተላለፉ/አሰራጩ።አዎ!፡አገር፡እና፡ሕዝብ፡የእሚያወድም፡የትግሬ፡ጎጠኛ፡አምባ፡ገነን፡ወራሪ፤ብሔር-ብሔረተ፡ሰብ፡በእሚል፡ያረጀ፡እና፡ያፈጀ፡**እስታሊናዊ፡**ፍልስፍና፡የእሚአወናብድበትን፡ልሠና፡ሥራ፡ነው፡እያሉ፡ይሚገቱለታል።**እስታሊን፡እኮ!፡በአካባቢው፡ዐቅመ፡ደካማ፡የነበሩ፡አገሮችን፡ወሮ፡ከሶቪዬት፡ዩኒዬን፡ጋራ፡ከቀላቀላቸው፡በኋላ፡በቋንቋ፡እና፡ቀሪ፡ባሕላቸው፡ምክንያት፡በኅብረት፡የማስተዳደር፡ችግር፡ስለ፡ነበረበት፡ነበረ።እንዲያም፡አድርጐ፡ሕልሙ፡ሳይሳካለት፡ቀርቷል።እንጂ፡ሙከራው፡እንደ፡እኛ፡ለብዙ፡ሺ፡ህ፡ዓመታት፡አብሮ፡በመስማማት፡የኖረውን፡ሕዝብ፡ጎሳ፡ከጎሳ፡እያጋጨ፡በመከፋፈል፡ለማኃደል፡አልነበረም**።እናም፡ወያኔን፡ካልደገፉ፡ችሁ፡ለአሳር፡ብለው፡እንሆ!ኢትዮጵያውያትን፡እና፡ኢትዮጵያውያን፡ባለሙያ፡ጋዜጠኞችን፡ይዘልፉሉ።ይወቅሳሉ።የፍኖተ፡ኅብረት፡ሕዝባዊ፡አገዛዝ፡(ዴሞክራሲ)፡ነፉስ፡ድምፅን፤የአዲስ፡ነፉስ፡ድምፅን፤የኢትዮጵያዊነት፡ነፉስ፡ድምፅን፡........ወዘተ፡በዚህ፡በዲ፡ሲ፡አካባቢያችን፡ያሉት፡እያሉ፡**ለኢትዮጵያ፡እና፡ሕዝቧ፡የቆሙ፡አገር፡እና፡ወገን፡ወዳዶችን፡ያውም፡እንደ፡እነሱ፡ሳይሆኑ፡የትግሬ፡ወያኔን፡ድጎማ፡አሻፈረን፡ብለው፡ቤታቸውን፡ሸጠው፡መሥዋዕት፡ለመሆን፡የተዘጋጁትን**።ሆነና፡አምባ፡ገነን፡ገዳዮችን፡ካልደገፉ፡ችሁ፡እያሉ፡ያወግዟቸዋል።የታሠሩትን፤በየቀኑ፡እየተደበደቡ፡በውጋት፡እና፡ቁርጥማት፡ለእሚሰቃዩት፡ወገኖቻችን፡መታሰቡ፡ቀርቶ፤በነፍሰ፡ገዳይ፡አረመኔነቱ፡የተጠላውን፡ወያኔ፡የለገሠ፡ዜናዊን፡እና፡ተወደው፡በዓለማት፡የተከበሩት፡የአመሪካ፡መንግሥታት፡ሙሴ፡ብሩክ፡ኦባማን፡ምሥል፡ይዘው፡የትግሬ፡ወያኔ፡መሪ፡ተብየው፡ለገሠ፡ዜናዊ፡ሆይ!ወገኖቻችንን፡በማስገደልዎ፤በኢትዮጵያችን፡ረሃብን፤ችግርን፤ሰቆቃን፡......በማንገሥዎ፤መሬቷን፡እየከፋፈሉ፡ለውጭ፡ዜጋዎች፡ኢትዮጵያውያት፡እና፡ኢት

ዮጵያውያን፡አርሶ፡አደሮች፡ያለሙትን፡እየቀሙ፡በመሸጥዎ፤ድንግል፡መሬት፡ለማልማት፡የውጭ፡ዜጋዎች፡ይጉዳሉ፡ብለው፡በማሰብዎ፤በኒቶ፡ሙሶሊኒ፡ኢትዮጵያችንን፡ለማጥፋት፡ዓቅዶት፡የነበረውን፡ለመፈጸም፡ስለ፡እሚጥሩ፡እንኮራብዎታለን።በማለት፡በአቶ፡ንጉሤ፡ቢራቱ፡አስተባባሪነት፡የኢትዮጵያውያት፡እና፡ኢትዮጵያውያንን፡መበደል፡እንዳይሰሙ፡የዓለማት፡መሪዎችን፡ግራ፡አጋብተው፡ሰልፉን፡ጠልፈውታል።የእኛዎቹም፤ከእኛ፡ጋራ፡ተባብረው፡ለአገር፡እና፡ወገኖቻችን፡ብሶት፡ማሰማት፡የተሰለፉ፡መስለዋቸው፡ከመንገድ፡ተቀላቀሉ።ሲያዩዋቸው፡ግን፡የሕዝብ፡ድምፅ፡እንዳይሰማ፡አደናጋሪ፡አሻጥረኞች፡መሆናቸውን፡ተገንዝበው፡አወገዟቸው፡፡ከዚያም፡በኋላ፡ሰልፋቸውን፡በመቀጠል፡የዕለቱን፡ተግባራቸውን፡አከናውነዋል።

አቶ፡ንጉሤ፡ቢራቱ፡የተባልከው፡ደግሞ፤የሀገር፡ፍቅር፡ነፋስ፡ድምፅ፡ዜና፡አዘጋጆች፡ጋብዘውህ፡የተናገርከው፡አወዛጋቢ፡መልስህ፤የታሪክ፡ባለቤት፡የሆኑትን፡አፄ፡ኃይለ፡ሥላሴን፡ትናንት፡ከተወለዱ፡አረመኔ፡አምባ፡ገነኖች፡ጋራ፡በዓለም፡አቀቀፍ፡ሥነ፡መንግሥት፡(ፖለቲካ)፡አስተሳሰብ፡ጉዳይ፡ላይ፡ማወዳደርህን፡ሰምተን፡እጅግ፡በጣም፡አዘንን።መጀመሪያ፡አንተ፡ማነህ?የእነ፡ሆደ፡አምላኩ፡ተባባሪ፡ነህ፡መሰለኝ።ማንም፡ምን፡ያድርጉ፡አፄ፡ኃይለ፡ሥላሴን፡የኢትዮጵያ፡ጠላቶች፤የታሪክ፡ደምሳሶች፡ከሆኑት፡እና፡ለሀገር፡እና፡ለሕዝብ፡ፍቅር፡ከሌላቸው፡ጋራ፡ማወዳደር፡መሞከርህ፡አድርባይ፡እነትህን፡የእሚገልጽ፡ስለሆነ፡ለወደፊቱ፡ይህንን፡ከመሰለ፡አድራጎት፡እና፡ዐውቃለሁ፡ብለህ፡ከመሳሳት፡ተቆጥበህ፤አጉብዳጅነትህን፡ብትቀጥል፡ይሻላል።ለገሠን፡ለማወደስ፡ጥቂት፡ሰወች፡አስከትለህ፡የመራኸው፡ሰልፍ፡የወያኔው፡እንደራሴዎች፡ተባበረን፡ብለው፡እንደ፡ሰበኩህ፡ይታመናል።ሰልፉን፡ላደራጀህበትም፡እንደ፡ተከፈለህ፡አንጠራጠርም።እናም፤የአሁኑ፡አታላይነትህ፡የመጀመሪያህ፡እና፡የመጨረሻህ፡እንዲሆን፡እንመኛለን።

## የሰው፡ውሻ፡በበላበት፡ይጮሃል፤ እንደ፡እሚባለው፤

ክቡራት፡እና፡ክብራን፡በስደት፡አገር፡የምትኖሩ፡ወገኖቻችን፡ሆይ!፡፡ለትዝብት፡እንዲሆናችሁ፡እንሆ!

ለሀገር፡ፍቅር፡የነፋስ፡ድምፅ፡ዜና፡አዘጋጆች፡የምንልከው፡መልእክት፤ከዚህ፡በፊትም፡የቤት፡ሥራችንን፡ሠርተን፡በሥጋዊ፡ከትግሬ፡ወያኔ፡አገዛዝ፡ጋራ፤በመንፈሳዊም፡ከሕግ፡አልባ፡በወያኔ፡ተመራጭ፡ጳጳስ፡ጋራ፤አገር፡እና፡ወገንን፡ለእሚጐዳ፡በአላችሁ፡ቅርብ፡ወዳጅነት፡የተሰማንን፡በኅዋ፡ሰሌዳ፡አስታውቀናችሁ፡ነበረ።ነገር፡ግን፡"እኛን፡የእሚቃወም፡ነቀፌታ፡በሙሉ፡እንደ፡ማር፡ስለ፡እሚጣፍጠን፡የፈለጉትን፡ቢሉ፡ከመደገፍ፡አንቆጠብም"።ስለ፡እምትሉ፡መብታችሁ፡ስለ፡ሆነ፡ደግ፡ብላችኋል።አሳባላችንን፡ግን፡እንድትገነዘቡልን፡የምንሻው፤የኢትዮጵያ፡እና፡የሕዝቧ፡ሕልውና፡ጉዳይ፡ስለ፡ሆነ፡ተቸግረናል።እና፡እኛን፡በመምሰል፡በችግራችን፡አትነጎዱ።መጥፎ፡ድርጊት፡ጊዜአዊ፡ስለ፡ሆነ፡ሲያልፍ፡ያስተዛዝባል።ዘመቻም፡የያዛችሁት፡እንደ፡እናንተው፡ጋዜጠኞች፡በሆኑት፡ወገኖቻችሁ/ን፡ላይ፡ነው።ቀደም፡ብላችሁ፡አብራችሁ፡ትሠሩ፡አልነበረም፡እንዴ?።፲፡ሺህ፡ብር፡ለዜና፡ማሰራጫ፡ሥራ፡ማካሄጃችሁ፡መቀበላችሁን፡ሰምተን፡አስታውቀናችሁ፡ነበረ።እናም፡ነፍሰ፡ገዳይ፡የትግሬ፡ወያኔን፡"አትናገሩት"፡ብላችሁ፡ለተጨባጭ፡ማስረጃነት፡እየመሰከራችሁ፡ነው።
ስለዚህ፤ሀገር፡ፍቅሮች፡ሆይ!፡ጋዜጠኛ፡ማለት፡ማስረጃ፡ሰብስቦ፡በአስተማማኝ/በተጨባጭ፡ምስክርነት፡ሕዝብ፡እንዲያውቀው፤ወገን፡ሳይለይ፡እና፡በገንዘብ፡ሳይደለል፡ባለማዳላት፡የመሥራት፡ሥነ፡ምግባር፡ያለው፡ስለ፡ሆነ፤እባካችሁ፡ቋንቋችሁን፡አስተካክላችሁ፡ዜና፡አሰራጩ፡እንላለን።ከጉጉል፡ያለውን፡ለእኛ፡የጋዜጠኛነት፡ሙያ፡ለሌለን፡ተውልን።

እርግጥ፡በእሚያሳፍረን፡ሁኔታ፡የኢትዮጵያ፡ቅድስት፡ተዋኅዶ፡ቤተ፡ክርስቲያናችን፡ተዋርዳለች።ቅርሷንም፡እያወደሙት፡ነው።የቤተ፡ክህነቷ፡ታላቅ፡ጉባኤ፡ፍርክስክሱ፡ወጥቷል።ለመፈረካከሱ፡አስተዋጽዎ፡አድርጓል፡የምንለው፡የአስተዳዳሪዋ፡ጉድለት፡እና፡ሙሰና፡ነው።በዚህም፡ምክንያት፡"የዓሣ፡ግማቱ፡ከአናቱ"፡እንዳሉት፡የበላይ፡ባለ፡ሥልጣናት፡ተጠያቂነት፡አለባቸው።ቤተ፡ክርስቲያናችን፡እንደዚህ፡በሆነችበት፡ወቅት፡ሁለት፡አብሮ፡አደግ፡ጳጳሳት፡ተብየወች፡ተጣልተው፡ጉዳቸውን፡ሲጉላጉሉ፡ሁኔታውን፡በሰላም፡ለመፍታት፡በመጣር፡ፈንታ፤ጋዜጠኞች፡ለአንዱ፡ድጋፍ፡እየሰጡ፡አጋኖ፡ማባባሱ፡የእሚያበሳጭ፡ነው።"ዝሆኖች፡ሲጣሉ፡የእሚረገጠው፡ሣሩ፡ጭምር፡ነው"።ነው፡እና፡ለአንደኛው፡ቄስ፡ድጋፍ፡ወያኔአዊ፡ቅስቀሳ፡ለምታካሄዱበት፡የእሚለግሷችሁ፡ስደተኞች፡ከመካከላችን፡ካሉ፡እንዲያሥቡበት፡እናሳስባለን።እናንተን፡መርዳት፡ማለት፡የወያኔ፡አገዛዝ፡ተብየው፡መሪ፡ለገሠ፡ዜናዊ፡እና፡በሕገ፡ወጥነት፡በወራሪዎች፡የጳጳሰ

ው፡ቈስ፡ገብረ፡መድኅን፤በአገር፡እና፡ወገኖ ቻችን፡ላይ፡ጥፋት፡ለእሚያውሉት፡ተባባሪ፡መሆናችሁን፡እንዳይዘነጉ።

ለሕዝባቸው፡የእሚበጅ፡ፍትሐዊ፡አስተዳደር፡የላቸውም፡በማለት፡የወዳጅ፡አገር፡መንግሥ ታትንም፡መሪዎች፡በማስተባበር፤ታላቁ፡አመሪካ፡በኩባ፡ላይ፡የምጣኔ፡ሀብት፡ማዕቀብ፡እያደረገ፡ነው።በኢራቅም፡ያደርግ፡ነበረ።በኢራንም፡እያቅማማ፡ነው።በሰሜን፡ኮርያም፡እንዲሁ።እነ፡ንጉሤ፡እና፡በላይ፡ግን፡ወያኔን፡ፈርተው፡ጥቅማቸው፡እንዳይጐድል፡ማዕቀብ፡መደረጉ፡የኢትዮጵያን፡ሕዝብ፡ይጐዳል፡በማለት፡አጐብዳጆች፡ናቸው።ለሕዝባችን፡በቀጥ ታ፡የእሚደርሰው፡ቢሆንማ፡ምን፡ግድ፡ነበረን።በኢትዮጵያ፡እና፡በሕዝቧ፡ስም፡የተለመነው፡ሁሉ፡ለትግሬ፡ልማት፡(መልማቱን፡መቃወማችን፡ሳይሆን፡አድልዎ፡መደረጉን፡ለማመልከት፡ነው)።እና፡ለጎሳዋ፡ማበልጸጊያ፡እና፡ለአረመኔው፡ወራሪ፡አምባ፡ገነን፡የትግሬ፡ወያኔ፡አገዛዝ፡ኪስ፡ስለ፡እሚገባ፡እንጂ።፡እናም፡ችግራችን፡የአስተዳደር፡መዛባት፡ነው።የኢትዮጵያን፡ዜጋዎች፡በእኩልነት፡የእሚያይ፡መሪ፡እንሻለን።መንግሥት፡ሳይኖር፡ሕዝቡ፡እራሱን፡በእራሱ፡እያጽናና፡እንሆ!፡፲፰፡ዓመ ታት፡አልፎ ታል።በቃ!፡ብሎ፡የእራሱን፡ሕዝባዊ፡አገዛዝ፡መሥርቶ፡እና፡መሪውንም፡መርጦ፤የምጣኔ፡ሀብቱን፤የሥነ፡መንግሥቱን፤የኅብረተ፡ሰቡን፡......ወዘተ፡ሥነ፡ሥርዓት፡አመቻችቶ፡ለመኖር፡መደራጀት፡አለበት።

በውጭ፡አገር፡እየተንከራተትን፡ያለን፡ወገኖቼም፡ድጋፋችንን፡መለገሥ፡አለብን፡እንጂ፡በኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡ችግር፡በማሳበብ፡የተጠራቀመውን፡መቀጨ፡ለግል፡ጥቅማቸው፡ለእሚያውሉ፡ጋዜጠኞች፡እና፡ምላሰ፡ቀልጣፋ፡ግለ፡ሰወች፡እንዲበዘብዙት፡አንፍቀድ።

## የሰንደቅ፡ዓላማ፡መከበሪያ፡ቀን፤



እንኳን፡የሣጥናኤልን፡ሰንደቅ፡ዓላማ፡ቀን፡በይፋ፡ለማክበር፡አበቃችሁ።የኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡ያላመነበትን፡መንግሥ ታዊ፡በዓል፤የትግሬ፡አምባ፡ገነን፡ወያኔአዊ፡ጦርነቶችን፤ሕዝባዊ፡መብቶች፡መገፈፍን፤የምክር፡ቤት፡ውሸት፡የበረከተሳቸው፡ድስኩሮች፡ማዳመጥን፤የበይ፡ተመልካችነትን፤ሕዝብ፡እየተራበ፡ድግሥ፡ደግሦ፡መፈንጠዝን፤የራስን፡ብሔራዊ፡ቋንቋ፡ንቆ፡እንግሊዝኛ፡መናገርን፤መገደልን፤መታሠርን፤መገረፍን፤ዕድገቱ፡ረሃብን፡የእሚያበረ ታ፡ምጣኔ፡ዳብሯል፡መባልን፤ተቀዳሚ፡ምሉክ፡(ፕራይም፡ምኒስትር)፡ያልፋልሉ፡እና፡በመንገድ፡ጀርባችሁን ወደ፡እርሳቸው፡አዙራችሁ፡ቁሙ፤...ወዘተ፡ኧረ፡ስንቱ!፡አክብረናል፡እኮ!

ይኸን፡ካልን፡በኋላ፡አቶ፡ንጉሤ!፡አንተ፡እንደዚህ፡ለጥፈህ፡ልሳችሁ፡ይብገን፡ለማለት፡የሞከርከው፡በከንቱ፡ነው።ለምን?፡ብትል፡አርቀህ፡ካለማሰብህ፡የተነሣ፡በራስጌህ፡የለጠፈከው፡ሥዕል፡ትርጉም፡ስለ፡ነበረው፡ለማውቅ፡አልፈለግህም።በትግሬ፡ወያኔዎች፡የተነገረህን፡"የብሔር-ብሔረሰቦችን፡እኩልነት፡አመላካች፡ነው፡ተብሎ፡ስለ፡ታመነ፡ነው"።የተባለልህን፡ከሆነ፡እነሱን፡ደስ፡ይበላቸው፡ብለህ፡ለማጐብደድ፡ተመቻችቶልሃል።እውነቱ፡ግን፡የቀድሞው፡አረንጓዴ፤ቢጫ፤ቀዩ፡እኩልነትን፡በተገባር፡ጀግኖ ቻችን፡ያሳዩበት፡ስለ፡ነበረ፡የትግሬ፡ወያኔዎችን፡ዓይን፡ስላሳመመ፡ማጥፋት፡ፈለገው፡ነው።እዚህ፡ላይ፡ልናሣሣስብህ፡የምንወደው፡በአንተ፡እና፡በትግሬ፡ወያኔዎች፡ላይ፡ጥላቻ፡አድሮብን፡እንዳይመስልህ።የጠላነው፡የኢትዮጵያ፡እና፡ሕዝቧ፡ሕልውና፡እየወደመ፡መሆኑን፡ጨክናችሁ፡ስትፈጽሙት፡የምናየውን፡ሥራችሁን፡ነው።ሀቁን፡ዕድሜ፡ከሰጠን፡ኃይላችሁ፡በሕዝብ፡ቁጣ፡ተሸንፎ፡በምናይበት፡ግዜ፡ይሆናል።ከዚህ፡ቀጥሎ፡የሣጥናኤላዊውን፡ዓላማ፡እና፡እውነተኛውን፡እኩልነት፡ገላጭ፡አርማ፡ትርጉም፡ለመግለጽ፡እንሞክራለን።

የጥሊያኑ፡አምባ፡ገነን፡የበኒቶ፡ሙሶሊኒ፡በኢትዮያ፡ላይ፡የነበረው፡ዕቅድ፡ከሸፎ፡ሰላም፡ከሰፈነ፡በኋላ፤

"ኢትዮጵያ፡ህገሬ፡ሞኝ፡ነሽ፡ተላላ፤
የሞተልሽ፡ቀርቶ፡የገደለሽ፡በላ"፤ ተባለ።

በቀኝ፡ጌታ፡ዮፍታሔ፡ንጉሤ።

# በሃይማኖት፡ካባ፤

## <u>የሚሠራ፡ደባ፤</u>

በገጽ፡፳፩፡ይምመልከቱ።

**በሊ.ቀ፡ምሁር፡ለይኩን፡ብርሃኑ፤**



ይህን፡ምልክት፡በመጽሐ ፉ፡አላካተቱም።

“በኢትዮጵያና፡በእግዚአብሔር፡መካከል፡እጅግ፡ብዙ፡ብዙ፡ጉዳዮች፡ተከናውነዋል።ተፈጽመዋል።እኒህን፡ሁሉ፡ድርጊቶች፡እናያለን።እናነባለን።ይህ፡ታላቅ፡ነው።በአጠራር፡ብቻ፡የዳዊት፡ኮከብ፡በሚል፡ሥያሜ፡እናውቀዋለን።ስለዚህ፡በዚህ፡ኮከብ፡ምሳሌነት፡ኢትዮጵያና፡አምላኳ፡ያላቸው፡ትስስር፡ማስረጃና፡መታወቂያ፡ነው።አስረጅነቱም፡ሰማይና፡ምድር፡አንድ፡ሆኑ፡ነው።”ሰማያት፡ይነግራ፡ስብሐተ፡እግዚአብሔር”።(ሰማያት፡እግዚአብሔርን፡ያመሠግናሉ።መዝ.18.1)እንደዚሁም፡”ስብሐት፡ለእግዚአብሔር፡በሰማያት፡ወሰላም፡በምድር፡ለእጓለ፡እመሕያው፡ሥምረቱ”።(ክብር፡ለእግዚአብሔር፡በአርያም፡ይሁን።ሰላምም፡በምድር፡ለሰውም፡በጎ፡ፈቃድ፡አሉ።ሉቃ.2.14)



ይህ፡የእናንተ፡አርማ፡ግን፡የዲያብሎስ፤የሣጥናኤል፡አምላኪዎች፡ስለሆነ፡ያለ፡አግባቡ፡ሰብካችሁ፡ሕዝባችንን፡ለስቃይ፡አትዳርጉት።ከእምነቱም፡አታፈናቅሉት።የምርጫ፡መብታችንንም፡አትንፈጉን።በሕዝባዊ፡አገዛዝ፡(ዴሞክራሲ)፡የምታምኑ፡ከሆነ፡እውነተኛውን፡ትርጉም፡ለሕዝብ፡ምርጫ፡አቅርቡት፡እና፡ሕዝብ፡ከተስማማበት፡እኛ የምንቃወምበት፡ግላዊ፡ወይም፡ጥቅማዊ፡ምክንያት፡አይኖረንም።

እግዚአብሔር፡እርስ፡በእርሳችን፡ከመነታረክ፡ይጠብቀን።ዓይናችን፡እያየ፡እና፡አዕምሯችን፡ማሰብ፡እየቻለ፤እኛ፡ብቻ፡የምንለውን፡ተቀበሉ፡የምትሉን፡ከሆነ፡ከእኛ፡በተሻለ፡ማስረጃ፡አቅርባችሁ፡እንጂ፡በደፈናው፡አስሱን፡ገሰሱን፡እያቀረባችሁ፡አታስጨንቁን።

አምላከ፡ኢትዮጵያ፡እሷን፡እና፡ሕዝቧን፡ይባርክ።ለመተባበርም፡ልቦና፡ይስጠን።አሜን።

ደህና፡እንሁን፡እና፡ለእሚቀጥለው፡እንገናኝ።